የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ — የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 22
ADDIS ABABA – 27th February, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፷፬/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
"ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የእርሻ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ .................... ገጽ ፫፻፶፯

## CONTENTS

Proclamation No. 64/1997
International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for partly Financing the National Seed Project Ratification Proclamation ...... Page 357

### አዋጅ ቁጥር ፷፬/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የእርሻ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፬ ሚሊዮን ፮፻ሺህ (አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የእርሻ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፮ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የእርሻ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 64/1997

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICULTURAL DEVELOPMENT

*WHEREAS,* a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Developement provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of four million six hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 4,600,000) for partly financing the National Seed Project, was signed in Rome, on the 11th day of October, 1996;

*WHEREAS,* the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 27th day of February, 1997;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for partly Financing the National Seed Project Ratification Proclamation No. 64/1997."

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የእርሻ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· አክቶበር ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፮ በሮም የተፈረመው ቍጥር ፬፻፳፩ ኢ.ት· የብድር ስምምነት ነው ።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬ ሚሊዮን ፮፻ሺህ ኤስ·ዲ·አር· (አራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 421–ET. signed in Rome on the 11th day of October, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of four million six hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 4,600,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 27th day of February, 1997.

Done at Addis Ababa, this 27th day of February, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE